# ስርነቀል ጉዞ ( Radical Journeys)
## ወንዶች በበላይነት ፖለቲካውን በሚቆጣጠሩባት ኢትዮጵያ ሴቶች ጸረ-አምባገነን ትግሉን እያፋፋሙት ነው

*በሬቸል ሉዊሰ*

*ትርጉም በሜሮን አሃዱ*

ካባ የደረበች በ 20 አመታት ውስጥ ያለች ወጣት፤ የተጠቀለለ ስጦታ ይዛ ጭቃማ ጉዳናውን አቅንታ ወደ ጉዳይዋ ቦታ ደረሰች። እንደርሷ በፈነደቁ አጃቢዎች ታድማለች። የሊዲያ ምረቃ ነው። ዘመድ አዝማድ ተሰብስቧል። ምግብና ደስታ አለ። ሊዲያ ስለወደፊት እጣ ፋንታዋ ከአዳሚዎቿ ጋር ስትመክር እናትየዋ እምባ ባቀረረ አይኖች በኩራት  ይተክዙባታል።

ከዚህ በፊት በምረቃ በዓል ላይ ለተገኘ ሰው ይህ አዲስ ነገር አይደለም። ይህን ምረቃ ልዩ የሚያደርገው ነገር ቢኖር ስነስርዓቱ የሚደረገው አዲስ አበባ በሚገኘው በቃሊቲ ፌደራል እሥር ቤት መሆኑ ነው። የሚከናወነውም ዘመድ እሥረኛን ሊጠይቁበት በተፈቀደችው አንዲት ሰዓት ውስጥ ነው።

ቃሊቲ እሥር ቤት ሰፋ ሰፋ ያሉ ቆርቆሮዎች የለበሱ የኮንክሪት ቤቶች ስብስብ ነው። ብረቶቻቸው ዛግ ዛግ ብለዋል። የጠዋቱን ውርጭ የፈረቀው የቀትር ፀሐይ ይለበልባል።እስረኞችና ጠያቂዎቻቸው የሚገናኙበት መሥመር ላይ ነው የሊዲያን ምረቃ እናቷ የምትካፈለው። ጌጣ ጌጦችና ማሸብረቂያ የለም። ዘፈንም ክልክል ነው። ዳሩ ግን አንዳንድ እምቢተኞች ማንጎራጎራቸው አልቀረም። ከመለስተኛው ድግስ የወዳደቀውን ለመቀራመት አይጦች ሃይለኛ ሽኩቻ ላይ ናቸው። ጥቂት ቆይቶ “10 ደቂቃ ቀራቹህ” የሚለው የጥበቃ አላፊው ማስጠንቀቂያ በሚቆራረጠው ማይክሮፎን ያቃጭላል። የምረቃውም ሥነሥርዓት በዚሁ ያከትማል። የተረፈውን ምግብና አገልግሎች በጥዲፊያ ይወሽቃሉ። ጠያቂና ተጠያቂ ይሰነባበታሉ።

ሊዲያና እናቷ ትይይ ቆመዋል። የስንብት ጊዜ ነው።እንደምንም ብላ ፈገግ ትልና እናትየዋ ልጇን ደጋግም እንኳን ደስ ያለሽ ትላታለች። ከእዴመዋ ብስለት በዘለቀ ሁኔታ ስሜትዋን ደብቃና ተቆጣጥራ እናቷን ተሰናብታ ትሄዳለች።

ይህ ምርቃት ለ 48 አመትዋ ወ/ሮ ንግስት ገብረሕይወት ያልተጠበቀ ፌሽታ ነው የሆነላቸው። ቃሊቲ እሥር ላይ ስለሆኑ በሐምሌ ወር 1998 የተካሄደውን የሊዲያ ምረቃ ላይ ሊገኙ አልቻሉም ነበርና። ወ/ሮ ንግስት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የስዕል

አስተማሪ ሲሆኑ እኝህ የሦስት ልጆች እናት፤ ባለፈው የምርጫ ውዝግብ ጊዜ የታወጀው የመንግስት አፈና ሰለባ ናቸው።

ለ 13 ወራት ከሌሎች 70 ሴቶች ጋር በጠባብ ክፍል ታጉረዋል። "ዘር ለማጥፋት ቅስቀሳ አድርገዋል፤ የአገር ክህደት ፈጽመዋል" ተብለው ተከሰዋል። "ጥፋተኛ" ከተባሉ የእድሜ ልክ እሥራት ወይም የሞት ፍርድ ቅጣት ሊፈረድባቸው ይችላል። አምንስቲ ኢንተርናሽናል እኝህን ወይዘሮና አብረዋቸው የተወነጀሉትን ተከሳሾች :" የሕሊና እስረኞች ... የታሰሩት በሰላማዊ መንገድ ተቃውሞዋቸውን ስለገለጹ ብቻ ነው " ይላል። ውጤቱ የሚጠበቀውን በብዙሃኑ የተወገዘውን ችሎት " በአለምአቀፍ ደረጃ የሚጠበቅበትን የፍትሕ መስፈርት ያላሟላ ...ተጽዕኖ ባለባቸው ዳኞች ፊት የቀረበ ፍርድ ." ሲል አምንስቲ አውግዞታል።

ወ/ሮ ንግስት እንደሌሎቹ እስረኞች እምብዛም ታዋቂ አይደሉም። ሲናገሩ እንደበታቸው ርትኡ ነው። መልዕክቶቻቸውም መልካሙን ያዘሉ ናቸው። "ሕዝቡ ለመብቱና ለነጻነቱ ያለውን ጽኑ ጥማት አይተናል። እነርሱ (መንግስትን ማለታቸው ነው) በዚሁ እንድንቀጥል ሊያስገድዱን አይችሉም።" ይላሉ አልበገሪቷ ወይዘሮ ንግስት። እንደእርሳቸው አመለካከት ችሎቱ ፍትህ ላይ እየተሳለቀ ነው። "እኛ ላይ ምንም ማስረጃ የለም። ምርጫውን ሕጉ በሚፈቅደው መንገድ ነው ያሸነፍነው። ከሕገ መንግስቱ ውጪም መንግስትን ለመገልበጥ አልሞከርንም። ማሸነፋችንን ብናውቅ እንኳን ከሥልጣን እንዲለቁ አልጠየቅናቸውም። እኛ ያነሳናቸው ነጥቦች ቢኖሩ የዲሞክራሲ መዋቅሮች እንዲዘረጉ፤ ባለፈው የምርጫ ጊዜ የነበሩት ጋሬጣዎች እንዳይደገሙ እንዲረጋገጥ ... " ብለው ይቀጥሉና " የእኛ ክስ የፖለቲካ ክስ ነው። ሕዝቡ ከእኛ ዘንድ ሲቆም ሲያዩ ነው የከሰሱን። እነርሱ እንደሆነ ሥልጣን ላይ ለመቆየት የማያደርጉት ነገር የለም።"

ወ/ሮ ንግስት የጸኑ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ናቸው። በአገር አቀፍ ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰብዓዊ መብት ረገጣን ለማጣራትና ለማጋለጥ የተቋቋመውን ኢሰመጉን ( ወይንም የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔን) ከመሰረቱት ሰዎች መካከል አንዷ ወ/ሮ ንግስት ናቸው። መንግስት ኢሰመጉን የተቃዋሚዎች መሳሪያ ነው በሚል እንደ ባላንጣ ጠምደው ነበር የያዙት። ወ/ሮ ንግስትም ካለ ፖለቲካ፤ ለውጥ ማምጣት ዘበት መሆኑን ከልምዳቸው አገናዝበው የመጥበሻ ድስት ወደሆነው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ገቡበት።

በ1997 ከመጀመሪያዎቹ የቀስተደመና ተምዝጋቢዎች አንዷ ነበሩ። ለቅንጅትም ተቀጥረው ሕዝቡን ከማደራጀታቸው ባሻገር ከነ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ጋር የምርጫ ዘመቻውን ንድፈ ሐሳብ በመቅረጽ ቁልፍ ሚና ተጫውተዋል። ባለቤታቸው በሞት ከተለይዋቸው በኋላ ብቸኛ የቤት አስተዳዳሪ የሆኑት ወ/ሮ ንግስት ወህኒ መውረድ ቤተሰባቸው ላይ ትልቅ የገንዘብ ጫና ጥሏል። በተለይም ደግሞ እየተባባሰ የመጣው

የሁለት ወንድ ልጆቻቸው መሸበር ወ/ሮ ንግስትን እያሳሰባቸው ነው። “ የእኔ መታሰር ልጆቼ በጣም ከብዷቸዋል። ይህን አይነቱን ኢፍትሃዊ ድርጊት ለመቀበል እጅጉን ያዳግታቸዋል። ሴት ልጄ እንኳን እራሷ እናት ሆናለችና የበለጠ እየበረታች ነው የመጣችው” ይላሉ ወ/ሮ ንግስት።

በአቅራቢያው ቢጫማ ቡኒ ኮት ያደረገች ሴት ልጅ ከእናቷ ጋር በትግሪኛ ታወራለች። የሰፈነውን ሃዘን በፈገግታዋ ሸፍነዋለች። ከወ/ሮ ንግስት ጋር ጠባቢቷን ክፍል ይጋራሉ። ከአንድ ልጇ ተነጥላ መኖር አዳግቷታል። የ 32 አመትዋ ወ/ሮ ሰርካለም ፋሲል ጋዜጠኛና የሦስት ዋና ብሄራዊ ጋዜጦች ባለቤት የነበረች ስትሆን ከአመት በላይ ተቀልፋለች።

<u>የወይህኒ ቤት ልጅ</u>

የ 4 ወረ ነፍሰ ጡር እያለች ነው ከባለቤትዋ ከአቶ እስክንድር ነጋ ጋር ዘብጥያ የወረደችው። መንግስትን በጽኑ የሚጻረር ዘገባዎችን በማውጣታቸው ነው ኢላማ የሁኑት። የጸጥታ ሃይሎች ጥቅምት 1997 ቢሮዋቸውን ከበረበሩ በኋላ በማግስቱ ሊያስሯቸው ወደ ባልና ሚስቲቱ ቤት ይሄዳሉ። እነርሱ ግን ቀደም ብለው ተሰውረዋል። ስዕላቸውን እንደ አደገኛ ወንጀለኞች በብሔራዊ ቴሌቭዥን አስተላለፈው። ሕበረተሰቡ እንዲያድናቸው ይጠየቃል። እናትየዋም ለ 5 ቀን ታግተዋል። በዚህ ሦስት ሳምንት በሞላው አደን ጊዜ ውስጥ ወንድሟ ታስሮ ተለቋል። አይቀሬ ነውና ካሉበት በጥቆማ ይደረስባቸውና ወደ ወህኒ ቤት ይወርዳሉ።

በአጸያፊው ቃሊቲ እሥር ቤት ነው እንግዲህ ወ/ሮ ሰርካለም ከባድ የሆነ እርግዝና ያሳለፈችው። የውርጭና ወበቅ መፈራረቁን፤ የቅማልና ተላላፊ በሽታዎችን መቋቋም ነበረባት። ሆኖም ግን ብርቱነቷ አልተለያትም። ፍርድ ቤት ከመመላለስም ወደኋላ አላለችም። ችሎቱ ሲሰፍር ምንም እንኳን እርግዝናዋ ሲገፋ እንድትቀመጥ ብትጠየቅም እንደሌሎቹ እሥረኞች ሁሉ ከመቀመጫዋ ብድግ ማለቷን አልተወችም። አምንስቲ እንደዘገበው ወ/ሮ ሰርካለም በቂ የሆነ የሕክምናና የወላድ እንክብካቤ እንዳታገኝ ተከልክላለች። የ24 ሰዓት ፖሊስ ጥበቃ እየተደረገባትም ነው ወንድ ልጇን በተወዳጅነቱ እንብዛም በማይታወቀው ፖሊስ ሆስፒታል የተገላገለችው። ለሁለት ሳምንት ብቻ ነበር ከልጇ ጋር እንድትቆይ የተፈቀደላት። የእናትና የልጅ ትስስር በሚጀምረበት በመታረዣና በመደሰቻዋ ጊዜ ነው እንግዲህ ሕጻኑ ከእርሷ ተነጥቆ ለዘመዶቹ የተሰጠው። የእናት ጡት የተነፈገው ጨቅላ ክፉኛ ታሞም ነበር። ከልጇ የተለይችውና ከባለቤቷ ጋር መሆን ያልቻለችው ወ/ሮ ሰርካለም አይምሮዋ ጨልሞባት ነበር።

መንፈሷ አሁን እየተነቃቃ መጥቷል። ልጇን መንከባከብ አለመቻሏ እስከአሁን ይቆጫታል።ስለሕጻኑ እድገትና ሁኔታ ማወቅ የምትችለው ጠያቂዎቿ በሚነግሯትና በሐሳቧ በምትቀርጸው ነው።

የእነዚህ ሁለት ሴቶች ጉዳይ ሊከሰት የማይችል በደል ሊመስል ይችላል። በዚች በሰሃራ በታች በምትገኝ አገር ( ዘጋቢዋ ኢትዮጵያን ማለቷ ነው) ብዙ ዘጋቢዎች እንደሚያመለክቱት ሁሉ የእንደዚህ አይነት ክስተቶች እየተበራከቱ መጥተዋል። በሺህ የሚቀጠሩ ሴቶች የአገዛዙን አስከፊ ገጽታም እየተቃመሱት ነው።

በአሁኑ ጊዜ ባለው የአለም አቀፍ የመንግስት አስተዳደር መመዘኛዎች በጠቅላይ ሚኒስትር መልስ ዜናዊ የሚመራው የኢሕአዴግ መንግስት በአለም ላይ አስከፊ ሙስናና ሕገወጥነት ከሰፈነባቸው መንግስታት የሚፈረጅ ነው። በሰብዓዊ መብት ረገጣና በሕጋዊ ፖለቲካ እንቅስቃሴ አፈናም በአለም አቀፍ ደረጃ የተወገዘ መንግስት ነው። የመንግስት ሃይሎች የሰብአዊ መብት ረገጣውን ከማባባስ በተጨማሪ ካለፍው ከተደረገው አወዛጋቢ ምርጫ ወዲህ የመናገር ነጻነት ላይ ጠርነት አውጀዋል። የውጭ ጋዜጠኞችን አባረዋል። ነጻ ጋዜጦችን አግደዋል። በሰኔና ጥቅምት በተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ ላይም ፖሊስ ያልታጠቁ ዜጎች ላይ ተኩስ ከፍቷል። ከ 193 በላይ ሰው ገድለዋል። በመቶዎች የሚቀጠሩን አቁስለዋል። ከሞቱት ውስጥ ወንድ፤ ሴት፤ ሕጻናት ይገኙበታል። ወደ 30 ሺህ ሰዎችን አፍሰው አጉረዃል። የአገሪቱን ተማሪዎች፤ መምህራን፤ የሕዝብ አገልጋዮች፤ ታዋቂ የሕዝብ መሪዎችንና አብዛኞቹን የቅንጅት አመራር ወደ ወህኒ አውርዷል።

እንዲህ ባንሰራፋው የመንግስት አፈና ግን ዲሞክራሲያዊ ትግሉ አልተቋረጠም። በትግሉም ሴቶች ትልቅ ሚና እየተጫወቱ ነው። እናቶች፤ አያቶች፤ ጠበቃዎች፤ጋዜጠኞች፤ መምህራን፤ ሃኪሞች የሕዝብ አገልጋዮች የፖለቲካ መሪዎች እየሆኑ ለወደፊቱ ትውልድ ፈር እየቀደዱ ነው።

አንዷ ታዋቂ መሪ የ 32 አመት ወጣቷ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ነች። ወ/ት ብርቱካን የቀድሞ የፌዴራል ፍርድ ቤት ዳኛና የቅንጅት ምክትል ሊቀመንበር ናት። እርሷም በጥቅምት 1998 ነው ወደ ወህኒ የወረደችው። ገና ለጋ በሆነው በ25 አመቷ ነው ለፓርላማ መቀመጫ የተወዳደረችው። ይህም በኢትዮጵያ ከመጀመሪያዎቹ ወጣት ሴቶች መካከል አሰልፏታል። ወ/ት ብርቱካን ገለልተኛ ሁና ነው በጸረ ሙስና አቋም የተወዳደረችው። ታዛቢያን እንደሚሉት የገዢው ፓርቲ ባያጭበረብራት ኖሮ ድል ተቀዳጅታም ነበር።

ወ/ት ብርቱካን በአገሪቱ ዝናዋን ያተረፈችው የቀድሞ የመከላከያ ሚኒስቴር (ዘጋቢዋ ስዬ አብርሃምን ማለቷ ነው) በሙስና በተወነጀለበት ጊዜ ነው። ይህ ክስ የተመሰረተውም በሕወአት ውስጥ ክፍፍል በተነሳ ጊዜ ነው። ክሱ የፖለቲካ

ጉዳይም ነው ይላሉ ታዛቢዎች። በዚህን ጊዜ ታይቶ በማይታወቅ ወኔ ወ/ት ብርቱካን ተከሳሹን (ስዬን መሆኑ ነው) ካለ በቂ ማስረጃ የዋስ መብቱን አልነፍግም ብላ በዋስ አሰናብተዋለች። ምንም እንኳን ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዋስ እንዳይለቀቅ ጫና ቢያደረግም ወ/ት ብርቱካን የፍርድ ቤቱን ገለልተኛነት ለማስጠብቅ ያደረገችው ተጋፍጦ በመላው አገሪቱ ትልቅ አድናቆትን አትርፎላታል። ለብዙሃኑም ትልቅ አርአያ ሆናለች።

ይህች ብርቱ ሴት ከፖለቲካ መድረክ ተባራ በቃሊቲ እሥር ቤት ከበርካታ ወንጀለኞች ጋር ጠባብ ክፍል ውስጥ ታጉራለች። የአገሪቱ ሁኔታ ከሐሳቧም ባይጠፋም የግል ችግሯም እያሳሰባት መጥቷል። ብቸኛዋ፤ የአረጂ እናትዋ፤ የእህቷና የሕጻን ሴት ልጇ አስተዳዳሪ  እንደመሆኗ መጠን የቤተሰቧ ችግር ብርቱካንን ያስጨንቃታል። ቤተሰቧ ለጊዜው የሚተዳደረው ከመታሰሯ በፊት ባጠራቀመችው ብርና ከቅንጅት ደጋፊዎች በሚያገኙት እርዳታ ነው። እናትየዋ እንደሚሉት " እሷ ያጠራቀመችው ሲያልቅ ምን እንደሚውጠን አናውቅም፡".

ከልጇ መለየቷ እየበላትና እየከበዳት መጥቷል። ከልጇ ተለይታ የምታሳለፈው እያንዳንዱ ቀን ብርቅዬ የሆነውን የልጅዋን ጨቅላ ዘመን እንዳታይ ነፍጓታል። ልጇ ሁሌ እሑድ ከሰዓት በኋላ ባለው የዘመድ ጥየቃ ጊዜ ትገኛለች። ከአስተያየቷ እሥር ቤት የምታያትን ሴት የምታውቃት ይመስላል። አያትየዋ ግን እናቷን እየዘነጋቻት ነው ይላሉ።

<u>የጥብቅና ድንቅዬ</u>

በአጭር በሆነው የሙያ ስምሪቷ የብርቱካን ተሳትፎ ጉልህ ነው። በሚያዚያ 1994 ላይ ባሳለፈችው ውሳኔ (ዘጋቢዋ የስዬን በዋስ የመልቀቋን ማለቷ ነው) እድገት ተነፍጓት በመቆየቷ ወ/ት ብርቱካን ወደ ግል ጥብቃና ሙያ ተቀላቀለች። የተሳካላት፤ ብቁና ተፈላጊነቷም የናረ ጠበቃ ወጥቷታል። ከባልደረቦቿ በላቀና በሚያሳፍራቸው መጠን ነጻ የጥብቅና አገልግሎት ትሰጥ ነበር። ባለፈውም ምርጫ አገልግሎቷን ለተቃዋሚ ክፍል ችራለች። ቀስተደመናንም እንድትቀላቀል ከተጋበዘች በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ አክብሮትንና አድናቆትን አትርፋ ወደ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተመርጣለች። ወዲያውኑም ለቅንጅት ምክትል ሊቀመንበርነት በመስከረም 1998 ተመርጣለች።

ወ/ት ብርቱካን ስለማህበረሰብ ያላት ግንዛቤ ጥልቅ መሆኑ ይመሰከርላታል። አልበገሬነቷ፤ ርህሩህነቷ፤ የሥራ ትጋቷ፤ የአመራር ብስለቷ (አቋመ ጽኑ ግን ግትር ያልሆነች) በብዙሃኖች ዘንድ ተወዳጅነትንና አድናቆትን አትርፎላታል። ለዚህ ምስክር የሚሆነው ብዙዎች እርሷ እሥር ቤት እንዳትወሰድ ሲፋለሙ መሰዋታቸው ነው። ወደ ፈረንሳይ ለጋሲዮን የሚገኘው የቤተሰቧ መኖሪያ ፖሊስ ሊያስራት

ሲወርድ በብዙ የሚቆጠሩ ሰዎች ግቢዉን ከበዉ ተከላክለዋል። እናትየዋ እንደሚያስታዉሱት “ ወዲያዉኑ ጎሮቤቶቻችን ብርቱካንን ሊከላከሉ መጥተዋል። ወታደሮችን በድንጋይ ሊያባርሯቸዉ ሞክረዋል”። ያንኑ ቀን ከሰዓት በኋላ ከታወቁት የሰብዓዊ መብት ተከራካሪና ከዋናዎቹ የቅንጅት መሪዎች አንዱ ከሆኑት ከፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ጋር ታስራለች። በማግስቱም ፖሊስ ወ/ት ብርቱካንን ይዘዉ ቤትዋን ሊፈትሹ ሲሄዱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች እቤቷ ተሰብስበዉ ጠበቋቸዉ። እርሷን ለማስፈታት በተፈጠረዉ ግጭት ፖሊስ ጥይት ተኩሶ 5 ሰዎችን ገድሏል። የበለጠ ደም እንዳይፈስ ወ/ት ብርቱካን ደጋፊዎቿን እንድትታሰር እንዲፈቅዱ ተማጽና ነዉ ፖሊስ ይዟት የሄደዉ።

ምንም እንኳን ከወንጀለኞች ጋር ሕይወትን ማሳለፍ “ፈታኝ ጊዜ ቢሆንም “ ወ/ት ብርቱካን ጽናቷና ያላት የአገር ፍቅር አልቀነሰም። ወንጀለኞቹም በየጊዜዉ የሚያደርጉት ሽኩቻ ሰለ ወገኖቿ ያላትን መልካም አመለካከት አልመረዘዉም። ጽኑ እምነት በሰዉ ልጆች ላይ አላትና “ የተሻለ ሕይወት ከተሻሉ ሰዎች ጋራ ዉጭ (ከእሥር ቤት ዉጭ ማለቷ ነዉ) አሉ “ እያለች እራሷን ታነቃቃለች። ጓደኞቿ እንደሚሉት የሚመስጥዋትን አርዕስቶች የሆኑትን የፖለቲካ ፍልስፍናና የሃይማኖት መጽሃፍትን በማንበብ ነዉ ብዙዉን የእሥር ጊዜዋን የምታሳልፈዉ። የወህኒ ቤቱ አስተዳዳር ክፉኛ ቢያስፈራራትም ሁለት መጣጥፍትን በእሥር ቤት ጽፋ በድብቅ ልታስወጣ ችላለች። በተለያዩ የአለም አቀፍ ብዙሃን መገናኛ ድህረገጾች (ወይንም ዌብ ሳይቶች) ላይም ወጥተዋል። የመጀመሪያዉ “ከቃሊቲ እሥር ቤት የሚል” ሲሆን የተጻፈዉም የማርቲን ሉተር ኪንግ ከሆነዉ “ደብዳቤ ከበርሚንግሃም እሥር ቤት” ጽሁፍ መንፈስ ነዉ። በጽሁፏም ስላሳለፈችዉ ሂደትና ጽኑ ስለሆነዉ የዲሞክራሲያዊ አገዛዝ ጥማቷን ጥርት ባለ መልኩ ታስቀምጣለች። ጽሁፏ ላይ እንደምትገልጸዉ “ በእርግጥ መታሰር አስከፊ ነገር ነዉ። ስለወገኖቼ ትግል ስሰማ ለሁላችን ብለዉ ገፈት ሲቀምሱ በጣም ያስከፋኛል። ከድሉ ቢቀርቡም የትግሉ ሜዳ መራቁ ይሰማኛል። ሐዘኔ ግን እዚህ ላይ ያቆማል። የኛ መታሰር የትግሉን መንፈስ አያጠፋዉም። በአንጻሩ ግን ይሄን የሚገፉ (የመንግስት ሃይሎችን ማለቷ ይመስላል) ወደ ጭፍን ጥላቻና ክብረቢስነት ዝቅ አድርጓቸዋል። በዚህ አፈና እንዲያዉም ከልባቸዉ ለነጻነትና ለእኩልነት የሚታገሉ ከየአቅጣጫዉ ብቅ ብቅ እያሉ ነዉ። በታሰርኩበት ቦታ ሆኜ ይህንን ሳስበዉ ሐሴት የሞላዉ እሥር ነዉ እላለሁ።”.

## <u>ለመብት የጸኑ ሴት</u>

እንደበታቸዉ ለስላሳ ቁመናቸዉ አነስ ያለዉ የ 52 አመቷና የ 5 ልጆች እናት ወ/ሮ ሙሉነሽ አበባየሁን ጠንካራ ሴት ማለት ያልተጠበቀ አገላለጽ ሊሆን ይችላል። እኚህ ሴት 7 ወር ሙሉ በፌደራል እሥር ቤት ክስ ሳይመሰረትባቸዉ ቆይተዋል። የደህንነትም ክትትል ሕይወታቸዉን ስጋት ላይ ጥሎታል። እኚህ የቀደሞ አስተማሪ ካላቸዉ የነጻነት ትግል ሚናና ከአገር ፍቅራቸዉ አልበገር ብለዋል። የኢትዮጵያ

ሰላማዊ ፖለቲካ ትግልም ያልተጠበቁ ጀግና ናቸው። እናት፤ ቤት አስተዳዳሪ፤ የተቃዋሚ አባልና የመንግስት ረገጣ ሰለባ ናቸው። ያደጉበት ጊዜ ፖለቲካው የወንዶች ብቻ ሙያ ተደርጎ በሚቆጠርበት ዘመን ነው። እኝህ ለዲሞክራሲያዊ ለውጥ የተሰው ሴትዮ በአገሪቱ እየተቀያየረ የመጣውን ሁኔታ ያሳያሉ። ምንም እንኳን እንግልቱ ቢጨምርም፤ የውጭ አገር ጥገኝነት ባይሳካላቸውም ወ/ሮ ሙሉነሽ ባገኙት አጋጣሚ ሁላ ከውጭ ጋዜጠኞችና የአለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ተከራካሪች ጋር ሃሳባቸውን ያለአንዳች ፍርሃት ለመግለጽ ወደኋላ አይሉም። እንደዚህ አይነት ነጻ ንግግር ኦፊሼል ባይሆንም በሞት ሊያስቀጣ በሚችልበት አገር ይህ ትልቅ የብርቱነት ምልክት ነው። ለምን የዲሞክራሲ ትግላቸውን እንደሚቀጥሉ ሲጠየቁ መልሳቸው ቀጥተኛ ነው። “አገሬን እወዳለሁ። ታሪኳንም እከታተላሁ። ሕገ መንግስቱም ሁሉም ዜጎች በፖለቲካው መሳተፍ እንደሚችሉ ይገልጻል። ይሄን ወረቀት ላይ ካሰፈሩት ለምን አያከብሩትም?”

ከምርጫው ሶስት ወረ በኋላ ወ/ሮ ሙሉነሽ በዝዋይ ፌዴራል እሥር በት (በብዙሃን የሚታወቀው ማጎሪያ ቦታ ወይንም በእንግሊዘኛ አጠራር ኮንሰትሬሽን ካምፕ) ከሌሎች 86 ሴቶች ጋር አንደ ክፍል ውስጥ ታሰረዋል። በስም ማጥፋት ዘመቻና ለሕግ ባለመታዘዝም ተወንጅለዋል። በእስራት ጊዚያቸው ብዙ እሥረኞች የአካል ጉዳት ሲደርስባቸው ከማየታቸው ባሻገር እርሳቸውም ሁለት ጊዜ ተጎሽመዋል። ብቻቸውንም በአንድ ክፍል ውስጥ እንዲወሰኑ የተደረገበትም ጊዜ ነበር። የእሥር ዘመናቸውን ሲያስታውሱ ያንቀጠቅጣቸዋል። የእሥር ቤቱን መጥፎ ምግባና አይጦች እንዴት የሴቶችን እግር ጣት ይነክሱ እንደነበረም ያስታውሳሉ። “ ውሃ ይሰጡናል፤ ሽሮ ወጥና እንጀራም ይሰጡን ነበር ... ግን እንጀራው አሸዋ ስለነበረበት ብዙ ጊዜ ልንበላው አንችልም ነበር ... የቀይ መስቀል ሰራተኛ ሊቀምስ መጥቶ ሊበላው አልቻለም ነበር” ይላሉ።

ከግማሽ አመት በላይ ሶስት የተለያዩ ቦታዎች ከታሰሩ በኋላ ነገሩን በራሳቸው እጅ ወስደው የአምስት ቀን ረሃብ የማቅም አድማ አድረገዋል። ጥረታቸውም እጅጉን ሕመም ውስጥ ስለጣላቸው ፖሊስ ሆስፒታል ውስጥ ለሁለት ቀናት ተኝተው ያለምንም ክስ ተለቀዋል። በማንኛውም ጊዜ ሊታሰሩ እንደሚችሉ የፍትህ ሚኒስቴር ማህተም የያዘ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ደርሷቸዋል።

ከእሰራትም ከተላቀቁ በኋላ ለ 30 አመት ካስተማሩበት የ 8ኛ ክፍል የዜግነት ትምህርት አስተማሪነት ተነስተው ወደ 4 ኛ ክፍልና ከሚኖሩበት ራቅ ካለ ትምህርት ቤት ተዘዋውረዋል። እዚያም ሆነው በተለይ ከዲያሪክተሩ ቅርብ ክትትል ይደርስባቸው ነበር። የትምህርት ቤቱም ሰራተኞች ወ/ሮ ሙሉነሽ ባላቸው የፖለቲካ ግንኙነት ፍራቻ አግልለዋቸዋል። አንድ ሰውዬም እርሳቸውን ስላነጋገረ ብቻ በፖሊስ ተደብደቧልም ይባላል።

የሥራዉንም ሁኔታ ሊቋቋሙት ስላልቻሉ ጡረታ ከመዉጣት ሌላ አማራጭ አልነበራቸዉም። ከድሮ ደሞዛቸዉ ግማሽ በሆነ ገቢ ቤተሰባቸዉን መደጎም ከብዷቸዋል። ባለቤታቸዉም በጤና መጓደል ምክንያት ጡረታ ወጥተዋል። ወ/ሮ ሙሉነሽ ከአስር አመት በፊት ወላጅ አልባ የሆነች ሕጻን አምጥተዉ የሚያሳድጓት ልጅ አላቸዉ። በዚህም ሁኔታ እስከ መቼ ትምህርት ቤት መላክ እንደሚችሉ ያሳስባቸዋል።

ወ/ሮ ሙሉነሽ ከእሥር ቤት መገላገላቸዉ እንዳስደሰታቸዉ ጥርጥር የለዉም። እስከአሁን ድረስ ግን ክትትልና እንግልት ይደርስባቸዋል። በዚህም ምክንያት በገዛ እራሳቸዉ እራሳቸዉን የቤት ዉስጥ እሥረኛ አድርገዋል። በጣም የሚያስቀጣቸዉ ነገር ቢኖር ቤተሰባቸዉ ላይ ያደረሰባቸዉ ጫና ነዉ። የፖለቲካ አመለካከታቸዉ ብዙዎቹን ዘመዶች እንዳይጠይቋቸዉ አድርጓቸዋል። ፖሊስ ሌሊት መጥቶ በድጋሚ ሲበትናቸዉ ላለማየት ልጆቹም ከቤት ሸሽተዋል።

ስለማይቀየረዉ የወደፊቱ የትግል ሂደት ሲያወሱ በሹክሹክታ ነዉ ፡" አሁን እንደማይዉ ዲሞክራሲ ወደ ኢትዮጵያ ቶሎ አይመጣም። ምናልባትም 100 አመት ሊፈጅ ይችላል። ደርግ ስላልተገበረዉ ዲሞክራሲ ሲለፍፍ ቆየ። ይህም መንግስት መጥቶ ምንም ተጨባጭ ለዉጥ አላየንም። ስለ ዲሞክራሲ አዉቃለሁ። እዚህ አገር ግን በተግባር አይሰራም። አንዳንዴም ልጆቼም ሆኑ የልጅ ልጆቼም አያዩትም ብዬ እፈራለሁ። ራዕያቸዉ እንደማይጨበጥ ቢመስላቸዉም ያላቸዉን ጽኑ አቋም አላንገዳግደዉም። " ሌላ ምን ሊሆን ይችላል። ገና ድሮ አስረዉኛል። ፊት ለፊት አወራለሁ። ለእራሴ እንደሆነ አልፈራም። ግን ልጆቼን ለማዳን እፈልጋለሁ። የእኔ ፖለቲካ እነርሱን አደጋ ላይ እንዳይጥልብኝ እሰጋለሁ" ይላሉ ጠንካራዋ ወይዘሮ

<u>ሴቶች የነጻነትን ትግል እየስፋፉት ነዉ።</u>

እነ ንግስት፤ ሰርካለም ብርቱካና ሙሉነሽ ሕጻናት ከእናታቸዉ ጉያ የማይነጠቁበት፤ የግልና ሰብዓዊ መብቶች ለሚከበሩባት አገር መነሳታቸው ለአስፈላጊዉ ግን ብዙዉን ጊዜ ለሚዘነጋዉ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ትግል የሴቶች ሚና ያለዉን አበይት ቦታ ይመሰክራል።

በሚያሳዝን ሁኔታ በአፍሪካ ቀንድ ሴት ሆኖ መፈጠር ብዙ ጊዜ እንደእርግማን ነዉ የሚቆጠረዉ። በዚህች ብዙ ሕዝብና ችግር በሞላባት አገር ሴቶች ልጅ ከማሳደግ በተጨማሪ ብዙዉን ጊዜ ከባዱን ሥራ ይጋፈጡታል። ብዙዉንም ጊዜ ብቸኛ የቤት አስተዳዳሪ ይሆናሉ። ብዙ ጊዜ በወንዶቹ ዱላ ይቀምሳሉ። የሴት ግርዛትና የመሳሰሉት የጎጂ ልማዶች ብዙ አገሮች ዉስጥ የተለመደ ነዉ። አሁን ያልችዉም ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ ልዩ አይደለችም። በገጠሪቱ ኢትይጵያ ሴት ልጆች ገና ከትዉልድ ጀምሮ ይጨቆናሉ። ብዙ ጊዜም የትምህርት እድል አይሰጣቸዉም።

በዚህም የተነሳ ጥሩ ሥራ አድጎ የማገኘት እድላቸው የመነመነ ነው። በቶሎም እራሳቸውን ለማስተዳደር ሲሉ ትዳር ውስጥ ይገባሉ።

ቀስ በቀስ ግን እነዚህ ሁኔታዎች እየተሻሻሉ እየመጡ ናቸው። በአዲስ አበባ እንደሚታየው ብዙ ሴቶች በሕዝብ አገልግሎት፤ በሕግ፤ በንግድ፤ በፖለቲካው ..ወዘተ እየተሰማሩ ነው። ከምርጫው በፊት እንደታየው ከሆነ በተለያዩ እድሜ ገደብ ያሉ ከየቦታውና ከየገጠሩ እየተመሙ መጥተው የተጠናከረውን የመራጭ ማስተማሪያ ሴሚናር የተከታተሉና በኋላም ለሰአታት በጠራራ ጸሐይ ተሰልፈው የመረጡ ብዙ ሴቶች አሉ። ይህ ግልጽ አደርጎ እንዳሳየው የብሄራዊ ዲሞክራሲ ትግል እንደተለመደው የተማረውና ደህና የሚባለው ህብረተሰብ ክፍል ትግል ብቻ አለመሆኑን ነው። የምርጫ ሳጥን እንዳይሰረቅ ብቻዋን ስትጠብቅ ያደረች ያለተማረች ሰራተኛ ታሪክ በየቦታው የነበረ ነው። ይህንን አይነት አራያም ተከትለው ቤተሰባቸውንና ሕይወታቸውን የሰው በሺህ የሚቆጠሩ ሴቶች በአገሪቷ ዙሪያ አሉ።

በቀጥታ እንደ አራቱ ሴቶች ወይንም በተዘዋዋሪ ባለቤቶቻቸው የታሰሩና የተገደሉ ሴቶች ኑሮን ለማሸነፍ ከሚጥሩት ከባህላዊ ሚናቸው ባሻገር የዲሞክራሲ ትግሉን ያጠናከሩ በብዙ የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ሴቶች አሉ። በየቤቱ የየራሱ የሆነ የጭቆናና የአልበገርነት ታሪክ አለ። በየቀኑ ልጆቻቸውን ለማየት እሥር ቤት የሚሄዱት አሮጊቶች፤ሥራዋን ለመስራትና ልጆቿን ለብቻዋ ለማሳደግ የምትሯሯጠው ብሩህ ሴት፤በድንገት ብቻዋን ሆና ቤተሰቧን ለማስተዳደር ተጨማሪ ገቢ የሚያስፈልጋት የመካከለኛ እደሜ ሴት አዲስ ሞያ ለመማር ስትፍጨረጨር፤ እነዚህ ታሪኮች በተደጋጋሚ መተረክ ያለባቸው ናቸው።